3. የዓመት እረፍት ፈቃድ ክፍያንና የሥራ ምስክር ወረቀት እንዲሰጥ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እንደተጠበቀ ነው ፀንቷል፡፡
4. የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ በዚህ መልኩ ተሻሽሎ የተወሰነ በመሆኑ ይኸው ታውቆ ተገቢው ይፈፀም ዘንድ የዚህ ውሣኔ ግልባጭም ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡
5. ወጪና ኪራሣ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ
መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 25317

ኀዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ጥቁር አባይ ትራንስፖርት - ዘርሑ ኃይሉ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ደሳለኝ አብርሃ - ጠበቃ ማስረሻ በላይ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአማራ ብ/ክ/መ/ በኮምቦልቻ ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረው የሥራ ውል ከሕግ ውጭ የተቋረጠበት መሆኑን በመግለጽ ወደ ስራው እንዲመለስ፤ ይህ ካልተቻለም በሕጉ መሠረት ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉትና እንዲሰናበት ይወሰንለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው፡፡ ስለዚህም ከሣሽ የጠየቀውን ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎት ይሰናበት ሲል ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል እና የተጠሪው ከውሳኔው በፊት መሞቱን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አመልካች የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ ለተቋረጠበት ተጠሪ ጥገኞች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39/2/ለ/ እና 110/3/ መሠረት ታስቦ የሥራ ስንብት ክፍያ ይሰጣቸው በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 8 ቀን 98 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤት ለተጠሪ ጥገኞች እንዲከፈል ያሉት ገንዘብ በሕጉ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ በገንዘቡ አሰላል ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ እኛም ይህን አቤቱታ መሠረት በማድረግ የተጠሪውን ወራሾች /ጥገኞች/ አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ክርክሩን አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ሕግ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 ነው፡፡ መወሰን ያለበት ነጥብም የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በመባሉ ምክንያት ለጥገኞቹ የሚከፈለው ክፍያ የሚሰላው እንዴት ነው? የሚለው ነው፡፡ የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሰራተኛ ሕግ ከደነገገው ውጪ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውሉ ሲቋረጥ የሥራ ስንብት እና ካሣ የሚከፈለው በአዋጁ አንቀጽ 40 መሠረት ነው፡፡ ሠራተኛው ክፍያው ሳይፈጸምለት የሞተ ከሆነ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 110/2/ ለተመለከቱት ጥገኞቹ እንደሚከፈል በአንቀጽ 39/2/ ተመልክቶአል፡፡ ሕጉ የዘረጋው አሠራር ይህን በመሰለ ሁኔታ በግልጽ የተቀመጠ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቱ የተከተለው አካሄድ ግን ከዚህ የወጣ ነው፡፡ ክፍያውን ያሰላው ሠራተኛው /ሟች/ በሥራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት እንደሞተ በመቁጠር ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በዋቢነት የጠቀሰው አንቀጽ 110/3/ የሚገኘው "በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ስለሚሰጡ ክፍያዎች" በሚለው በአዋጁ በምዕራፍ ሦስት ስር ነው፡፡ አንቀጽ 110/2/ በአንቀጽ 39/2/ የተጠቀሰውም በሥራ ውል ከሕግ ውጪ መቋረጥ የተነሳ የሚከፈለው ክፍያም በስራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች በሚሰጡት ክፍያዎች ዓይነት ይሰላል ለማለት ታስቦ ሳይሆን፣ የሟች ጥገኞች ተዘርዝረው የሚገኙት በአንቀጽ 110/2/ በመሆናቸው ነው፡፡ ስናጠቃልለው ከሕግ ውጪ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ በሞተ ጊዜ ለጥገኞቹ ክፍያ የሚፈጸመው በአዋጁ አንቀጽ 39/2/ እና 40 መሠረት እንጂ በአንቀጽ 110/3/



መሠረት እንዳልሆነ በሕጉ በግልጽ ተመልክቶ ስለሚገኝ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በአማራ ብ/ክ/መ/የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08881 ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ለተጠሪ ጥገኞች የሚሰጠውን ክፍያ በተመለከተ የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ለተጠሪ ጥገኞች የሚሰጠው ክፍያ መሠላት ያለበት በአዋጁ አንቀጽ 39/2/ እና 40 መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ክርክር /የሰበር/ ምክንያት የደረሰ ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

   በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ለስር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ